ዛሬ ምሽት የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ መ/ቤት በ 2020 ወደ እስራኤል ለገቡ አዲስ ገቢ ተማሪዎች መስከረም 1 የሚጀምረውን የትምህርት ዓመት ምክንያት በማድረግ ለተማሪዎች "ኦሊም ኪታ" በሚል ርዕስ ልዩ ዝግጅት አድርጓል።
እ.ኤ.አ በ 2020 በዓለም ዙሪያ ከ 2,200 በላይ ልጆች ወደ እስራኤል ገብተዋል። በሚመጣም ማክሰኞ ወደ እስራኤል የትምህርት ስርዓት የመጀምሪያ ምዕራፋቸውን ይጀምራሉ።
ይህን ትልቅ ቀን አስመልክቶ የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ መስሪያ ቤት ላትሩን አካባቢ በሚገኘው ሚኒ እስራኤል በተባለው ቦታ አስተማሪና አዝናኝ የሆነ ዝግጅት አካሂዷል።
በዝግጅቱ ከቀድሞዋ ሶቬየት ህብረት፣ ከኢትዮጵያ፣ ከፈረንሳይ፣ ከሰሜን አሜሪካ እና ደቡብ አሜሪካን ጨምሮ ከበርካታ የተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ 120 ልጆች ተሳትፈዋል። ልጆቹ በራሳቸው ቋንቋ ተናጋሪ አስጎብኚ ቦታውን ጎብኝተዋል፣ በሰርከስ ትርዒት ተደስተዋል ፣ እናም ለመጪው የትምህርት ዓመት ስጦታዎችንም ተቀብለዋል።
ዝግጅቱ የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ ሚኒስተር ወ/ሮ ፕኒና ታምኖ እሸቴ በኮሮና ምክንያት በለይቶ ማቆያ ስለሚገኙ በቪዲዮ ቀርፀው በላኩት ሰላምታ እና መልካም ምኞት እይታ እንዲሁም የመስሪያ ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት ተጀምሯል።
ለሁሉም የእስራኤል ልጆች በእስራኤል ውስጥ በሚገኙ መዋእለ ህፃናት እና ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን ለሚጀምሩ መልካም እድልን እንመኛለን!!